# ከብዙ ደካማ አንድ ጠንካራ

ከአርባ ሸንበቆ አንድ ቀርቀሃ፣
ከአርባ ስንጥር አንድ ብትር

ሸንበቆ በመልኩ ቀርቅሃን ቢመስልም ጥንካሬ የሌለው፣ውስጠ ባዶ፣በውስጡ ሸረሪትና ትላትል ሊመሽግበት የሚችል፣ለምርኩዝም ሆነ መከተው አደጋን የማይከላከሉበት፣በቀላሉ ሊሰባበር የሚችል፣ከሳጣራና ቅርጫት ከመሆን በላይ ጥቅም የማይሰጥ ተክል ነው።
በአንጻሩ ቀርቀሃ በመልክ ሸንበቆን ቢመስልም ውስጠ ሙሉና ደንዳና፣ለቤት ማገር፣ ለእጅ ምርኩዝና መከላከያ ሊሆን የሚችል ጠንካራ የሚያስተማምን እጽዋት ዘር ነው።
ስንጥርም እንደዚሁ ምንም እንኳን የእንጨት አካል ቢሆንም ከመንደድና አመድ ከመሆን በስተቀር ለቋሚ ተግባር የማይውል የእንጨት ገለባ ነው።በተመሳሳይም ብትር ምንም እንኳን እንደ ስንጥሩ የእንጨት ዘር ቢሆንም በደንዳናነቱና ጠንካራ በመሆኑ ለምርኩዝም ሆነ የተሰነዘረን ዱላ መክቶ ለመከላከል ብሎም ለማጥቃት የሚያስችል ቀላል መሳሪያ ነው።
ከዚህ በላይ ያለውን ትንተና ከተቀበልን ሸንበቆም ሆነ ስንጥር በብዛት ቢሰበሰቡት ከሸክም ያለፈ አንድ ቀርቀሃ ወይም አንድ ብትር የሚሰጠውን አስተማማኝ አገልግሎት ያህል መስጠት አይችልም።
በተመሳሳይ ደረጃ ይህንን ምሳሌ በአገራችን የፖለቲካ አሰላለፍ ብንተረጉመው ለቁጥር የሚያዳግቱ አያሌ ድርጅቶች በየፈርጁ ተሰልፈው እናገኛለን። በስልጣኑ ዙሪያ ያሉትን ትተን በተቃዋሚው ዙሪያ ያሉትን ብንመለከት የትኞቹ ጠንካራ፣የትኞቹ ደካማ እንደሆኑ ለመመርመር የሚያስችለን መለኪያ በተግባር ያመጡት ውጤት ይሆናል።በተጨማሪም ለምን ዓላማ እንደቆሙና፣ ለወደፊት ሊያመጡ የሚችሉት ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ከሁሉም በላይ አደረጃጀታቸውንና መመሪያ ዓላማቸውን በማየት ማወቅ ይቻላል።
በትግሉ ሜዳ የተሰለፉትን ለማወቅ ከአደረጃጀታቸው ብንነሳ፣በሁለት እረድፍ እንደተሰለፉ እንገነዘባለን፤ በአገር አቀፍና በጎሳ መልክ በአገር አቀፍ መልክ የተደራጁት ምርሃግብራቸው ቢመረመር አብዛኛዎቹ ከትንሽ ስልታዊ ልዩነት በስተቀር ለተመሳሳይ ዓላማ የተነሱ ናቸው።ሁሉም በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የማያወላውል አቋም አላቸው።የህን ዓላማቸውን በተግባር ለመተርጎም ግን አልቻሉም።
ከመተባበርና አንድ ከመሆን ይልቅ እርስ በርሳቸው በግልና በቡድን ጥቅም፣የበላይነት ሽኩቻ ተጠምደው የቆሙለትን ዓላማ ዘንግተው እራሳቸውንና ቆመንለታል የሚሉትን ህዝብ በተደጋጋሚ ለአደጋ አጋልጠው መስጠታቸውን ባሳለፉት ታሪካቸው እስከ አሁንም ድረስ ለመመልከት ችለናል።አልፎ ተርፎም የሸረሪት መሰግሰጊያ እንደሚሆነው ሸንበቆ የወያኔ ሰርጎ ገብ እየገባ የሚበትናቸው ወይም በቁጥጥሩ ስር የሚያደርጋቸው ሆነዋል።ይህ አካሄዳቸው እስካልተለወጠ ድረስ የተሻለ ውጤት ያመጣሉ ብሎ መጠበቅ የህልም እንጀራ የሆናል።
በጎሳ ጎራ የተሰለፉት ደግሞ የጋራ ጸባያቸውና አንድ የሚያደርጋቸው በአትዮጵያ አንድነት ላይ ያላቸው አፍራሽ አቋማቸው ነው።
ከአገራዊ ጥቅምና ህልውና ይልቅ የጎሳን ጥቅምና ህልውና ቅድሚያ በመስጠታቸው ምንም እንኳን በተለያየ ስም ቢጠሩም የመጨረሻ ግባቸው ቋንቋን መሰረት ያደረገ ክልላዊ ነጻ መንግስት ማቋቋም ነው። ለዚህም ዓላማ በመጀመሪያው ወቅት ላይ አሁን በስልጣን ላይ ካለው የወያኔ ቡድን ጋር አብረው የታገሉ፣ ህገመንግስቱን የነደፉ፣እስከተወሰነም ጊዜ ድረስ ስልጣኑን ተካፍለው የቁዩ ናቸው።
የተለያዩበት ዋና ምክንያት አብረው የነደፉትን የመገንጠልን መብት የሚያውቀውን ህገመንግስት በተግባር እንደ ኤርትራው የሻእቢያ ቡድን አላስከበረልንም፣ የምንፈልገውንና ህገመንግስቱ የሚፈቅደውን የመገንጠል መብታችንን ሙሉ ለሙሉ አላሚላልንም ብለው በቅሬታ በተቃዋሚነት የተሰለፉ ናቸው። ካለው ስርዓት አራማጆች በዓላማም ሆነ በአደረጃጀት የተለዩ አይደለም፤እነሱም ጎሳን፣ ቋንቋንና ክልልን ማእከል ያደረገ አደረጃጀት የሚከተሉ ናቸው።አንዳንዶቹ ይህንን ዓላማቸውን በተራዘመ ስልት ከግቡ ለማድረስ ወያኔ የሚከተለውን የክልልና ጎሳ ፌዴሬሽንን ተሸክሞ ለመዝለቅ ወስነው የሚንቀሳቀሱ ናቸው።ይህ ደግሞ ህዝቡን ሊያስተባብርና ሊስብ የሚችል፣እምነት የሚጣልበትና ተስፋ የሚሰጥ፣አገሪቱንም ወደተሻለ አቅጣጫ የሚወስድ ሳይሆን ይበልጥ ቅራኔና ቀውስ የሚጋብዝና የሚያመጡት ለውጥ ያው በገሌ ወይም ከድጡ ወደማጡ የሚከት ነው።በመሆኑም በህዝቡ ህሊና ውስጥ ስጋትና ፍርሃት ከመውለዱ ባለፈ የብዙሃኑን አወንታዊ ድጋፍና እምነት የሚያስገኝ አየደለም።
በስልጣን ላይ ያለውንም ሆነ በዚህ የተቃዋሚ ጎራ ስር የተሰለፈውን ቡድን አንድ የሚያደርገው የጋራ አቋም ቢኖር ኢትዮጵያን እንደ አንድ አገር ሳይሆን የተለያዩ አገሮች በግድ ተሰብስበው የተፈጠረች አገር ወደፊትም በዚህ መልኩ ካልሆነም ተበታትና በጎሳ መንግስታት እንድትተዳደር አድርጎ የማየቱ ችግር ነው።በዚህ አስተሳሰብ ላይ የተነደፈው

ፖለቲካ በህገመንግስት የተደነገገውን የመገነጣጠል መብት በሂደት እውን ማድረግ ሲሆን እስከዚያ ድረስ በተገኘው መንገድ የወታደራዊ፣ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚካዊና ማህበረሰብአዊ አቅማቸውን መገንባት ነው።
የሚመሩበት ጽንሰሃሳብ በክልል የጠበበ በመሆኑ እንወክለዋለን የሚሉት ህዝብ የእኛ ነው ብለው ከፈጠሩት ክልል ውጭ ወይም በ«ከልላቸው» ከሚኖረው ህዝብ ጋር ለዘላለም እየተጋጬ ለሚኖርበት ዕድል የሚዳርግ ነው። ጎሰኝነት በትንሽነት አጥር ውስጥ የተከረቸመ ዓላማ የሚከተል ስለሆነ ለዓለም አቀፍ ግንኙነት ቀርቶ ለአገራዊ የህዝብ ግንኙነት የተመቼ አይደለም። መሃል ሰፋሪ የሆነው ሌላው የጎሰኞች ድንኳን ደግሞ በስልጣን ላይ ያለውን ቡድን እየተቃወመ ግን የነደፈውን አደገኛና ጸረ አንድነት፣ ጸረ ኢትዮጵያ ህገመንግስት ተቀብሎ በጎሰኞች ታጅቦ ሌላው ቀርቶ ከማንኛውም ጸረ ኢትዮጵያ አቋም ካለውም የውጭ ሃይል ጋር ሳይቀር ተባብሮ የስልጣኑ ባለቤት ለመሆን ሌት ተቀን የሚሰራው ቡድን ነው።ይህም ቢሆን ለአገሪቱና ለህዝቡ የዘላቂ ሰላምና የዲሞክራሲ ባለቤት አያደርግም።ብሎለት ስልጣን ቢይዝ አሁን ካለው ቡድን የተሻለ አይሆንም፤የስም እንጂ የይዘት ልዩነት የለውም፤ ቀልቀሎ ስልቻ ስልቻ ቀልቀሎ ነው።በጣም የሚያሳዝነው ነገር በዚህ ስብስብ ዙሪያ የተሰለፉት ቀና አገር ወዳዶች አባላትና ደጋፊዎች የድርጅቱ መሪዎች እንዳሻቸው ከተገንጣይ የጎሳ ድርጅቶች ጋር ሲፈራረሙ ለምንና በምን ላይ ስምምነት እንደደረሱ ጠይቆ ለመረዳት ቆራጥነት ሳይኖራቸው በጭፍኑ እያጨበጨቡ መቀበላቸው ነው።ደፍሮ የሚጠይቀውንና አካሄዳቸውን የሚቃወመውንም ከስነምግባርና ከኢትዮጵያዊ ጨዋነት በወጣ መልኩ ለማሸማቀቅና ጸጥ ለማድረግ ከወያኔ ካድሬ ባልተለየ መልኩ ያዙን ልቀቁን ሲሉ የተሰበሰቡበት ድርጅት ስልጣን ላይ ሳይወጣ እንዲህ ያለ ባህል የሚከተል ጭፍራ ይዞ ስልጣን ላይ ቢወጣ በተቃዋሚው ላይ ምን ሊያደርስ እንደሚችል ሲያስቡት ያስፈራል፣ይዘገንናል። ስለሆነም« ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም፣ወይም ተቀምጠው የሰቀሉት ቆመው ማውረድ ያዳግታል»የሚለውን አባባል እያሰቡ ከአሁኑ አደጋውን ማየትና ማሶገድ በድርጅቱ ውስጥ ካሉት አገር ወዳዶች ይጠበቃል።
ወያኔን በመጥላት ብቻ ከወያኔ ባልተለየ መልኩ የተደራጀን ስብስብ መከተልና መርዳት የጥፋቱ አካል መሆን ነው።ብልህ ሁለት ጊዜ አይታለልም፤ደጋግሞ የሚታለል የዋህ ሳይሆን ከጅል የባሰ ነሆለል ነው! የሚለውን ቃል ማሰቡ ይረዳል።
በጎሳ ተዋረድ ከተደራጁት በኩል ለአገር የሚበጅ ነገር ባይጠበቅም አገር አቀፍ እራእይ አንግበው የተሰለፉት በራሳቸው ድክመት እንደሸንበቆውና እንደ ስንጥሩ እንኳንስ በህዝቡ ላይ የሚደርሰውን በራሳቸውም ላይ የሚሰነዘረውን ጥቃት የሚከላከሉ አልሆኑም።
እርስ በርሳቸው ሲሻኮቱ እንቃወመዋለን ለሚሉት አገር አጥፊ ቡድን በተዘዋዋሪ ዱላ ከማቀበል በተረፈ ህዝብ እምነት የሚጥልባቸው አልሆኑም«ያህያ ባል ከጅብ አያስጥልም እንዲሉ» እነሱም በተደጋጋሚ የጥቃቱ ሰለባ ሆነዋል።።ይህንን ድክመታቸውን ሊያርሙና በአንድነት የመጣውንና ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ማሶገድ ይኖርባቸዋል።
ከዚህ በኋላ እንዴትና ወዴት?
የሚቀጥለውን የትግል አቅጣጫ ለመተለም ያለንበትን ሁኔታ መገንዘብና የትግሉን ደረጃና ቅደም ተከተል ማጤን ተገቢ ነው። በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ኢትዮጵያን በታትኖ ለመጥፋት እቅድና ፍላጎት እንዳለው በራሱ አንጋፋ መሪዎቹ አንደበት በተደጋጋሚ በአደባባይ ተገልጿል።ከሚሰራውና ከሚነገረው ብንነሳ አገራችን ኢትዮጵያ እንዳገር የመቀጠሏ ተስፋ እየመነመነ መምጣቱን እንገነዘባለን። የተቃዋሚ ጎሰኞችም ፍላጎት ተመሳሳይ ነው።ይህን ከተረዳን የመጀመሪያ ትግላችን አገር የማዳኑ ትግል ይሆናል ማለት ነው።አገር የማዳኑ ትግል የሚካሄደው ደግሞ የኢትዮጵያን አንድነት በሚቀበሉና በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑት ወገኖች«አገርህን አድን»በሚለው መርሆ ስር ተሰባስበው በሚፈጥሩት የጋራ ግንባር ስር መሰለፍ ሲችሉ ነው። የተለያዩት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚገኙ አገር አቀፍ የፖለቲካና የብዙሃን (የሙያ፣የእምነት፣የጾታ፣የሰብአዊ መብት ወዘተ)ድርጅቶች፣በአገር ውስጥ በየከባቢው የሚካሄዱት ህዝባዊ ትግሎች፣ ትግላቸውን ማቀናጀት ይኖርባቸዋል።ሁሉም በሚያመቸውና በሚችለው መንገድ ለጋራ ትግሉ የሚረዳውን ማበርከት ይገባዋል።ለዚያ ደግሞ የጋራ አመራር ለመፍጠር መስማማትና ጊዜ ሳይወስዱ ተግባራዊ ማድረግ ለነገ የማይሉት ተገባር ነው።የዚህ ግንባር የመጀመሪያው ግዳጅ በየቦታው የሚኖሩት ኢትዮጵያውያንን መብትና ደህንነት ማስከበር ነው።ህዝብ እንዳይፈናቀል፣እንዳይጠቃ መከላከል ነው።ይህን ማድረግ ለአገሪቱ አንድነት መሰረት ይሆናል።የተለያዩት ድርጅቶች በፖለቲካ መስመር የተነሳ ሲነታረኩ የኖሩበትን ልዩነታቸውን ወደጎን ትተው በዚህ አገር አድን ትግል ውስጥ የአገራዊ ግዳጃቸውን ሊፈጽሙ ይገባል።
እምቢ ብለው እስከዛሬ ድረስ በሚከተሉት አሰራር እንቀጥላለን ካሉ ተከታያቸውም ሆነ ታዛቢው ብዙሃን የሚሰጣቸውን ድጋፍ ሊነፍጋቸው ይገባል።የድርጅት ጥቅም ከሃገርና ከህዝብ ጥቅም አይበልጥም።ከአሁን በኋላ በድርጅት ላይ ድርጅት፣በስብሰባ ላይ ስብሰባ፣በሰልፍ ላይ ሰልፍ እያካሄዱና እርስ በርስ እየተጠላለፉ መሄድ መቆም አለበት።የህንን ደግሞ ሊፈጽም የሚችለው በየድርጅቱ ስር የተሰበሰበው አገር ወዳዱ ዜጋ ነው።የፍርሃትን ግንብ ጥሶ ድርጅቶቹን ሊጠይቅና ወደ አገር አድኑ ትግል እንዲገቡ ማስገደድ አለበት። በፉክክር ለየአዳራሹ ኪራይ፣ለዝግጅቱ፣ለመጓጓዣ የሚወጣው ገንዘብ አገር ቤት ውስጥ ለሚካሄደው ትግል ቢውል የበለጠ ውጤት ይኖረዋል።
በማህበረሰብ መካከል የሚኖር ልዩነት በመተሳሰብና በመወያየት የሚወገድ እንጂ በአምባጓሮና በግጭት የሚፈታ አይደለም፤ግጭትና ጥላቻ ሌላ ግጭትና ጥላቻ ይወልዳል።የጎሳና የእምነት ልዩነትን የፖለቲካ መዘውር ካደረጉት ማቆሚያ

ወደ ሌለው ግጭትና ማህበራዊ ቀውስ ብሎም አገር መበታተን አደጋ ይወስዳል።

የዩጎዝላቪያን፣የሶማሊያን፣የሩዋንዳን፣የብሩንዲንና አሁን በደቡብ ሱዳን የሚካሄደውን የእርስ በርስ እልቂት ጎሰኝነት ያመጣው ጣጣ ነው። ጎሰኝነት የፋሽዝም መፈልፈያ ቀፎ ለመሆን እንደሚችልም በአገራችን በኦነግ፣ በወያኔና በተለያዩ ጎሰኞች የተፈጸመውና በመፈጸምም ላይ ያለው ኢሰብአዊ ግፍ ማስረጃ ነው።የጎሰኝነትን አደጋ ቀደም ሲልም ከሂትለር አነሳስና ከፈጸማቸው ተግባሮች ለመረዳት እንችላለን።ሂትለር የአርያን ዘር ብሎ በመነሳት የዚያ ዘር ያልሆነውን የሌላውን አገር ህዝብ ቀርቶ የራሱን አገር ዜጋ ጀርመናዊውን ጭምር ጨፈጨፈው፣በጋዝ አፍኖ ጨረሰው።ዩጎዝላቪያም የሁለቱ ጸረሰላምና አንድነት ጠሮች፣የጎሳና የሃይማኖት ሰለባ ሆና መበታተኗን ብዙዎቻችን የምናውቀው አሳዛኝ ታሪክ ነው።በሃይማኖት ሰበብም በክርስቲያኑ መካከል እንዲሁ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት ተባብሎ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በሰለጠነው ያውሮፓ መሬት፣በአየርላንድ፣በአፍሪካም የዩጋንዳው« የአምላክ ሰራዊት» ብሎ እራሱን የሰየመውና የብዙ ወጣት ህይወት የቀሰፈው ቡድን፣ በእስልምናውም አልካይዳ፣አይሲስ፣ ቦኮሃራም፣አልሸባብ...ወዘተ እስከአሁን ድረስ በያገሩ በአላህ ስም በአላህ የሚያምነውን ጭምር እያረደው ያለው በሃይማኖት ስም ነው። በኢራቅ፣በሲሪያ ፣በየመን... ሱኒትና ሽይት እየተባባለ በየቀኑ የብዙ ሰው ደም ይፈሳል።

የጎሳ ተኮር ድርጅት ጎሰኝነትን ለሚቃወሙት የጎሳው ተወላጆችም አያዝንም።ለዓላማው እንቅፋት እንደሆኑ ስለሚቆጥራቸው በመጀመሪያ የሚያጠፋቸው እነሱኑ ነው።ስለሆነም የራሴ ጎሳ ነው ብሎ መዘናጋትና እያጨበጨቡ ከመደገፍ ይልቅ ቆም ብሎ ማሰብና አደጋውን በማጤን ለመከላከል ከጎሳ በላይ ሰብአዊነትን አብልጦ በማየት ከሌላው ጋር አብሮ መሰለፍ እራስን ከአደጋ ማዳን ነው። አገርንም ከመበታተን አደጋ ያድናል። አሁን ያለው ሁኔታ« ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ» የሚለውን አባባል የሚያመላክት ነው።

አገሪቱን ተቀራምቶ ለመሄድ ቢላዎ ስሎ የመጠባበቁ ሁኔታ፣የአንዱን ክልል ከሌላው ጋር የመዋዋጡ ወይም በሃይል የማቀላቀሉ አዝማሚያ አልፎ አልፎ በገሃድ ታይቷል።የወልቃይት፣በአፋር፣ በሶማሌና በኦሮሞ ክልል መካከል የታየው ግጭትና የህዝብ መፈናቀል የዚያ ማስረጃ ነው።የዚያ አይነት ፍላጎት ባይኖር ኖሮ በየጎሳውና ክልሉ ስም በትጥቅ መደራጀቱ ለምን አስፈለገ? አገራችንን የመቀራመቱ ፍላጎት በቅርበት ያሉትም ደቃቃ አገሮች ፣ጅቡቲ፣ሰሜን ሱዳን፣ደቡብ ሱዳን፣ኤርትራ ፣ ኬንያም ሳትቀር በዝግጅትና በጉጉት የሚጠብቁት ሴራ ነው።በርቀት ያሉት እንደ ኢጅብት፣ሳውዲና የመሳሰሉት ደገሞ ሃይማኖትን ተገን አድርገው የሚያገለግሏቸውን በማደራጀትና በመርዳት ላይ ናቸው። አገራችን ዙሪያ ከበባ ውስጥ ገብታ ትገኛለች።ያንን ከበባ ሰብሮ መውጣትና አደጋውን ተባብሮ ማስገድ አገራዊ ፍቅርና ስሜት ያለው፣ከትንሽነት ይልቅ ትልቅነትን የሚመርጥ፣በራሱ የሚተማመን ዜጋ አላፊነት ነው። ከመንደር እስርቤት የትልቅ አገር ባለቤት መሆን ለብዙ ነገር ይጠቅማል።ከስደት፣ከድህነት ከውርደት ያድናል።ስልጡንነትና ዘመናዊነትም ነው።ከእጅ አዙር አገዛዝና ባርነትም ያድናል።በታሪክና በትውልድም የሚያኮራ ስራ ነው።የጎሳና የሃይማኖት ልዩነቶችን መሰረት አድርጎ የሚነሳ እንቅስቃሴና መደራጀት አጥፊና ጎጂ መሆኑን የተረዱትና ያለፉበት የአፍሪካ አገሮች በተለይም ሩዋንዳ በህገመንግስት አጥብቀው ከልክለዋል።ጋናም ውስጥ እንዲሁ የጎሳና የእምነት እንቅስቃሴ በህግ የተከለከለ ነው። እኛስ በህግ ለመከልከል የግዴታ በስቃዩና በቀውሱ ውስጥ ማለፍ አለብን ማለት ነው?በጭራሽ መሆን የለበትም።ጉዳቱን ከሌሎቹ አይተን በመማር ቀድመን ልንገታው ይገባል።የዚያ መጀመሪያ ለጎሰኞች እውቅና አለመስጠት ነው።

በታሪካችን እንዳየነው የቅርብና የሩቅ ጠላቶቻችን ሊገቡ የሚችሉበት ቀላሉ መንገድ በጎሳ ድክመታችን ላይ ነው። ጎሰኞችን የገንዘብና የፖለቲካ ድጋፍ በመስጠት በትእቢት ትከሻቸው እንዲያብጥ አድርገዋል።ወደፊትም ስልጣኑን እንዲይዙ ያላሰለሰ ድጋፍና እውቅና በመስጠት ላይ ናቸው። አሁን ደግሞ ሃይማኖትን ተገን በማድረግ ተጨማሪ ወጥመድ እንደዘረጉብን መካድ የለብንም።

ቀጣዩ ትግል ከዚሁ አገር አድን ትግል ጋር በቀጣይነት ተያይዞ የሚከናወነው ትግል የስርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ትግል ነው።ይህ ትግል በፖለቲካ ድርጅት መልክ ተደራጅተው በሚያምኑበት ፍልስፍና መርሃግብር(ፕሮግራም) ነድፈው በሚንቀሳቀሱት መካከል የሚደረግ የሰላማዊ ትግል ሂደት ነው።ሃሳብን በነጻ አንሸራሽሮ ህዝብን አሳምኖ የስልጣኑ ባለቤት ለመሆን የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠርና በዚያው ለመጠቀም የመሳሪያ ግብግብና ደም መፋሰስ አይጠይቅም።የሚጠይቀው በዓላማ በልጦ መገኘትና ህዝብን ማሳመን፣ መቻቻልንና የሌላውን መብት እንደ እራስ መብት ማየትና አክብሮ መቀበል ነው።ለዚያ ዕድል ለመብቃት መንደርደሪያው በአገር አድኑ ትግል ውስጥ የተሳተፉትና ለድል የበቁት ሃይሎች የሚፈጥሩት የሽግግር ወቅት (መንግስት)ይሆናል።

ይህ የነገው ስራ ከዛሬው የአገር አድን ትግል በኋላ የሚከናወን ነውና ፊታችንን ወደ ቀዳሚው ትግል እናዙር።ለዚህ ትግል የየከባቢው ተወላጆች በሚያውቁት ቦታ፣ የማህበረሰብ ስነልቦና፣ቋንቋና ባህል ህዝቡን በመቀስቀስ የአገር አድኑ ትግል አካል እንዲሆንና አሁን በየቦታው የሚታዩት ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች እጅ ለእጅ ተያይዘው አገር አቀፍ እንቅስቃሴ እንዲሆኑ በሚያበቃው ተግባር ላይ ተደራጅተው መንቀሳቀስ

ይኖርባቸዋል።የገንደር፣የጎጃም፣,የወሎ፣የሸዋ፣የወለጋ፣የኮንሶ፣የጋምቤላ....ወዘተ እያሉ ተነጣጥለው መጓዝ ይጎዳቸዋል እንጂ አይጠቅማቸውም። ለጋራ ጥቅምና ደህንነት የግድ እጅ ለእጅ ተያይዘው ትግላቸውን ማስተባበር ይኖርባቸዋል።አንዱ ጠፍቶ ሌላው ተርፎ በሰላም እንደማይኖር መታወቅ አለበት። በአንድ ወቅት ላይ ጥቃት ያስመረረው ገበሬ የህብረትን

አስፈላጊነትና ጥቅም፣የመለያየትንና እርስ በርስ የመጠፋፋትን አደጋ በነዚህ ምክር ለበስ ግጥሞች አስተላልፏል።

**እንረስ ካላችሁ ተስማምተን እንረስ፣**
**የሁላችንም ቤት አንድ ላይ አይፍረስ።**
**የማን ቤት ፈርሶ የማን ሊበጅ፣**
**ያውሬ መፈንጫ ይሆናል እንጂ።**
አዎ!በተያዘው መንገድ መቀጠል ይህንኑ አደጋ መጋበዝ ይሆናል።
የፖለቲካ ድርጅቶችንና ትግሉን በሚመለከትም መቃወም ብቻ ፖለቲካ እንዳልሆነ መገንዘብ ጠቃሚ ነው።ፖለቲካ የህብረተሰብን አኗኗር፣ታሪክ፣ባህል፣እድገት በሳይንሳዊ ፍልስፍና መነጽር እየመረመረ ለተከሰቱና ሊከሰቱ ለሚችሉ ችግሮችና የተፈጥሮ ፈተናዎች መፍትሄ ለመጠቆምና ለማምጣት የሚያስችል ችሎታን የሚጠይቅ ሙያ ነው። ፖለቲካ ከሳይንስና ሂሳብ ጋር የተያያዘ መሆኑን ዶር ፈፋዱ በቀለ በሚያዝያ 24 ቀን 2017 «ፖለቲካም እንደ ሳይንስና እንደ ሂሳብ መታየት ያለበት ወይስ ሳይንስ አልባ»በሚለው ሰፊ ጽሁፋቸው ያቀረቡት ሲሆን መመልከቱ ይበልጥ ግንዛቤ ይሰጣል።።በሳይንስ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተና የተነደፈ የፖለቲካ መስመር ለአንድ አገር ህዝብ የሚያገለግል ከመሆን አልፎ በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚኖሩ የዓለም ህዝቦችም የሚረዳ ስለሚሆን ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ይኖረዋል።ስለሆነም በፖለቲካ መስክ ውስጥ የተሰለፉት የሚያዩበት መነጽርና የሚሰጡት መፍትሄ ከየትኛው ፍልስፍና በመነሳትና ለየትኛው የማህበረሰብ ክፍል ጥቅም እንደቆሙ የሚታወቁበት ማስረጃ ነው።በግልጽ በሚደረግ ውይይት የፖለቲካ ድርጅቶቹ ፍልስፍና መታወቅ ስለሚችል ድርጅቶቹ ሳይፈሩ ለውይይት፣ለትችትና ለነቀፋ መዘጋጀትና በር መከፈት ይኖርባቸዋል።

በዝግ አዳራሽ ከህዝብ ጀርባ የሚያጸድቁትና የሚፈራረሙት ውልና ስምምነት መኖር አይገባውም። ይህ አይነቱ አሰራር የድርጅቱን ችሎታና ትዕግስት ብሎም ታማኝነት ያበስራል።ውይይትና ትችት የሚፈራ፣ጭፍን ድጋፍ ብቻ የሚያሳድድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ስብስብ ወይም በጭፍኑ የሚደግፍ ጭፍራና ተከታይ የዲሞክራሲ ጠላት ነው።ይህ አይነቱ ደግሞ የተሻለ ስርዓት ያመጣል ማለት ዘበት ነው፤ የሚያመጣው ለውጥ ቢኖር የጅራፍና የገራፊ ለውጥ ብቻ ይሆናል።
አገርን ከመበታተን ለማዳን ከጎሰኞች ነጻ የሆነ " የኢትዮጵያውያን አገር ወዳዶች ግንባር" በአስቸኳይ ይመስረት!!
ኢትዮጵያ አገራችን ለዘላለም ትኑር!!
አገሬ አዲስ
ግንቦት 14 ቀን 2009 ዓ ም (23-05-2017)